# መመሪያ ቁጥር 148/2016

# የህብረተሰብ የአካባቢ ጥበቃ ተሳትፎ እና ስምሪት አፈፃፀም መመሪያ

ታህሳስ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ በህብረተሰብ ተሳትፎ የአካባቢን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ እየተጠናከረ የመጣ አዎንታዊ ተግባር መሆኑ እና ይህን ተሳትፎ ማጠናከር በማስፈለጉ፣

የህብረተሰቡ ተሳትፎ ከሚገለጽባቸው መንገድ አንዱ በህዝብ መዋጮ የአካባቢ ሰላምና ደህንነት የሚጠብቁ ቅጥር ጥበቃ አካላት ቀጥሮ ማሰራት አንዱ መሆኑ እና የእዚህ ጥበቃዎች ቅጥር እና ስምሪት ወጥነት የሌለው በመሆኑ በከተማ ደረጃ በጥበቃ ላይ የሚሳተፉትን ለመለየት፣ ስምሪት ለመስጠትና ለማስተዳደር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀፅ 15 (2) (ሠ) እና 40 (3) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የህብረተሰብ የአካባቢ ጥበቃ ተሳትፎ እና ስምሪት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 148/2016" ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. **"ኮሚሽን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ነው፤
4. **"ብሎክ"** ማለት በስሩ መንደሮችን ያቀፈ ከቀጠና በታች የሚገኝ የነዋሪዎች አደረጃጀት ነው፤
5. **"ቀጠና"** ማለት በወረዳ ውስጥ የተለያዩ ብሎኮችን እና መንደሮችን የያዘ አደረጃጀት ነው፤
6. **"የብሎክ ካውንስል"** ማለት 8 አባላት ያሉት ሆኖ በብሎክ ውስጥ የአስተሳሰብና የአኗኗር አንድነትና ውህደት ያላቸውን ነዋሪዎች ማዕከል ያደረገ የአገልግሎት አሠጣጥ፣ የአካባቢ መሠረተ ልማት፣ የደንብ መተላለፍ ቅድመ መከላከል እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚያከናውን ነው፤
7. **"አካባቢ ጥበቃ አባል"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በብሎክ ጥበቃ ላይ የሚሳተፍ፣ በህብረተሰቡ የሚመለመልና በብሎክ ካውንስል የሚሰማራ ሰው ነው፡፡
8. **"የጥቅም ግጭት"** ማለት ጥበቃው ከተሰጠው ኃላፊነት ውጪ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ለግልም ይሁን ለቡድን ጥቅም ሲባል ግጭት ሊፈጥር የሚችል ተግባር ውስጥ መግባት ነው፤
9. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ ያሉት የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ነው፤
10. **"ሚስጢር መጠበቅ"** ማለት የሥራ ባልደረባን ወይም የብሎክ ነዋሪውን ሊጎዱ የሚችሉ መረጃዎችን በሚስጢርነት መያዝ፣ በሙያና በሥራ ምክንያት የሚያውቁትን መረጃ እና በሕግ ሚስጢር ነው ተብሎ የተደነገገን ጠብቆ ማቆየት ነው፤

11. **"የህብረተሰብ ሰላምና ፀጥታ ተሳትፎ"** ማለት የብሎክ ነዋሪዎች የአካባቢያቸውን ሰላምና ፀጥታን ለማረጋገጥ በየተራ አካባቢን መጠበቅ፣ መረጃ መስጠት፣ ለጥበቃ ክፍያ መክፈል፣ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት መስጫ ማዕከል እና የጥበቃ ማማ መገንባት፣ በእውቀት እና በጉልበት እንዲሁም በመሳሰሉት ተግባራት አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት ነው ፤

12. **" A አካውንት"** ማለት ለአካባቢ ልማትና ለጥበቃ ከህብረተሰቡ የተሰበሰበ ገንዘብ በሂሳብ መደብ ቁጥር 6324 አካውንት ተከፍቶለት ሥራ ላይ የሚውልበት አሰራር ነው፤

13. **"ከህብረተሰብ የሚሰበሰብ መዋጮ"** ማለት ከብሎክ ነዋሪዎች የሚሰበሰብ እና ወደ "A" አካውንት ገብቶ ለጥበቃ ክፍያ የሚውል ገንዘብ ነው፤

14. **"የጸጥታ አካላት"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ እና የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ናቸው፤

15. **"የሰላም ሰራዊት"** ማለት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በመንደር፣ በብሎክ እና በሌሎች አደረጃጀቶች በመታቀፍ እና ከመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመቀናጀት የአከባቢያቸውን ሰላምና ጸጥታን የሚያረጋግጡ ኃይሎች ናቸው፤

16. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

17. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በህብረተሰብ በሚሰራ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች እና በጥበቃዎች፣ ብሎክ፣ ብሎክ ካውንስል፣ ጽ/ቤት እና በሂደት በሚሳተፉ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 4. የአካባቢ ጥበቃ አባላት መከተል ያለባቸው መርሆዎች

የአካባቢ ጥበቃ አባላት የሚከተሉትን መርሆች ተከትለው መስራት አለባቸው፡፡

1. ሥራን በተነሳሽነት እና በኃላፊነት መፈጸም፤
2. ከወንጀል ድርጊቶች የጸዳ መሆን፤
3. ለተመደቡበት ዓላማና ተልዕኮ ተገዥ መሆን፤
4. ለሥራው ታማኝ እና ሚስጥር ጠባቂ መሆን፤
5. ለህብረተሰቡ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት፤
6. ለህብረተሰቡ ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት፤
7. የህብረተሰቡን ባህል እና እሴት ማክበር፣
8. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት፣

9. የስራ ስምሪት በሚሰጡ አካላት የሚሰጠውን አቅጣጫ መከተልና መረጃ ልውውጥ ማድረግ፣

10.የስራ መመሪያ እና ስነ ምግባር አክብሮ መስራት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የህብረተሰብ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች እና መመልመያ መስፈርቶች

### 5. በአካባቢ ጥበቃ ላይ በሚሳተፉ ሰዎች የሚከናወኑ ተግባራት

የአካባቢ ጥበቃ ሆነው የሚመደቡት ሰዎች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጡ ይጠበቃል፡፡

1. በብሎክ በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰሩ መሰረተ ልማቶች ጉዳት እንዳይደርስባቸው መጠበቅ እና ጉዳት ያደረሱ አካላት ካሉ ተጠያቂ ማስደረግ፤
2. በብሎክ የእሳት፤ ጎርፍ እና ሌሎችም ድንገተኛ አደጋዎች ሲከሰቱ ለነዋሪዎች ማሳወቅና መከላከል፤
3. ከነዋሪዎች የሚሰጡ ጥቆማዎችን መዝግበው ችግሩን ለመፍታት መስራት፣ ከአቅም በላይ ሲሆን ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፣
4. በአካባቢው ካሉ ፖሊስ ፣ ሰላምና ጸጥታ፣ ደንብ ማስከበር እና ከሌሎች የጸጥታ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፤
5. በብሎክ ግጭት እንዳይፈጠር ማድረግ፣ ከተፈጠረም ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት በአፋጣኝ መፍታት፤
6. በብሎክ ለጸጥታ አስጊ እንቅስቃሴ ሲኖር ከብሎክ ካውንስል እና ከጸጥታ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፤
7. የብሎክ ነዋሪዎች በህገ ወጦች ጥቃት አንዳይፈጸምባቸው መጠበቅ፤
8. ለህጻናት፤ ለአቅመ ዳካሞች እና ለአካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት ሰጥተው መስራት፣
9. በብሎክ ደረጃ ለመረጃና ለምስክርነት ሲፈለጉ ተገቢውን መረጃ መስጠት፣
10. በየተራ አካባቢያቸውን ከሚጠብቁ ነዋሪዎች /ሮንድ/ ጋር በቅንጅት መሥራት፣
11. አዋኪ ድርጊቶችን ለይተው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለብሎክ ካውንስሎች እና ለሚመለከተው የጸጥታ አካል ጥቆማ መስጠት፣
12. በብሎክ ያሉ የህዝብ ወይንም የመንግስት ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ጉዳትና ስርቆት እንዳይፈጸምባቸው መጠበቅ፤

13. በብሎክ የፀጥታ ስጋት የሆኑ ቦታዎችን ለሚመለከተው አካል ጥቆማ መስጠት፤
14. በብሎክ የሚደረጉ ህገ ወጥ የመሬት ወረራዎች፣ ህገ-ወጥ ግንባታዎች እና ሌሎች የደንብ መተላለፍ ተግባራትን ለመከላከል ለሚመለከተው አካል ጥቆማ መስጠት፤
15. የቅጥር ጥበቃዎች አጋዥ ኃይል ሆነው ከመስራት አልፎ መደበኛ የፖሊስ እና የሌሎች የፀጥታ አካላትን ሥራ ተክተው አለመስራት፤

## 6. በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች መለያ መስፈርት

1. የሚከተሉትን መስፈርቶችን የሚያሟሉ ሰዎች በአካባቢ ጥበቃ ስራ ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡

   ሀ/ ዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ/ች/፣

   ለ/ በህግ የበላይነት የሚያምን/የምታምን/፣

   ሐ/ መልካም ስነ-ምግባር ያለው እና ከስካር፣ ከሱሰኝነት፣ አእምሮ ከሚያደነዝዙ እፆች ነፃ የሆነ/ች/፣

   መ/ በግል ባህሪውና በስነ-ምግባሩ ጥሩ የሆነ ቢቻል በህብረተሰቡ ውስጥ ባለው ተሳትፎ የሚታወቅ እና የምትታወቅ በማንኛውም የወንጀል ድርጊት የማይጠረጠርና ከዚህ በፊት ያልተሳተፈ/ች/ ወይም በክስ ሂደት ላይ ያልሆነ/ች/፣

   ሠ/ ዕድሜ ከ18 አመት ያላነሰ እና ከ65 አመት ያልበለጠ፣

   ረ/ ማንበብና መፃፍ የሚችል/የምትችል፣

   ሰ/ ለአካባቢ ጥበቃ ስራ የሚያበቃ አካላዊ ብቃት ያለው/ያላት፣

   ሸ/ ሙሉ ጤነኛ መሆኑ/መሆንዋ በህክምና የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል/የምትችል፣

   ቀ/ በአካባቢ ጥበቃ ስራ ላይ በሚሰጠው ስምሪት ተገዢ የሚሆን/የምትሆን፣

   በ/ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን ተግባራት ለማከናወን እና ከተከለከሉ ተግባራት ለመቆጠብ ፈቃደኛ የሆነ/ የሆነች፣

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች መለያ ዝርዝር መስፈርት በብሎክ ካውንስ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

## 7. በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሰማሩ ሰዎች መብት

በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች የሚከተሉት ግብዓቶች እንዲመቻችላቸው መደረግ አለበት፡፡

1. ስለሚሰራው ሥራ በቂ ግንዛቤ መስጠት፤
2. ለሥራ የሚያስፈልጉ ግብአቶች፤
3. በህብረሰተቡ ከሚደረግ መዋጮ የማበረታቻ ክፍያ የማግኘት፤

4. ላደረጉት አስተዋፅዖ መረጃ (ድጋፍ ደብዳቤ) የማግኘት፣

**8. ለአካባቢ ጥበቃ የሚውሉ ግብአቶች አቅርቦት**

1. በአካባቢ ጥበቃ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች የሚደረግ ማበረታቻ ከብሎክ ነዋሪዎች እና ከብሎክ ጥበቃው ተጠቃሚ ከሆኑ ተቋማት የሚሰበሰብ መዋጮ ይሆናል፤
2. ገንዘቡ በብሎክ ካውንስል አመራሮች በህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን በተዘጋጀው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብቻ ይሰበሰባል፤ የተሰበሰበውም ገንዘብ በዕለቱ ወደ "A" አካውንት ገቢ ይደረጋል፤
3. የአካባቢ ጥበቃዎች ማበረታቻ በወረዳው የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት በኩል ፔሮል ይዘጋጅ እና በብልክ ካውንስሉ ስራው መሰራቱን ሲታመን ክፍያው ይፈፀማል።
4. የአካባቢ ጥበቃ የደንብ ልብስና ሌሎች ግብአቶችን በህብረተሰቡ መዋጮ ወይም በህረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ከማእከል እስከ ወረዳ ባለው አካል ፕሮጀክት ተቀርጾ ከሚገኝ ገቢ ሊሸፈን ይችላል።

## ክፍል ሦስት

## የተከለከሉ ተግባራት እና የሚወሰዱ እርምጃዎች

**9. የተከለከሉ ተግባራት**

በአካባቢ ጥበቃ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች የሚከተሉት ተግባራት የተከለከሉ ናቸው።

1. ከአካባቢ ጥበቃ መመሪያዎች ወይም ከሚሰጡ ስምሪቶች ውጭ መስራት፣
2. ከሌሎች ጋር ተስማምቶ አለመስራት፣
3. በህገ ወጥ ድርጊት ላይ መሳተፍ፣
4. በብሎክ ውስጥ የተለያዩ የሰላም ማወክና የደንብ ጥሰቶች ሲፈጸሙ በቸልታ ማለፍ፤
5. ለብሎክ ነዋሪዎች ፍትሃዊ አገልግሎት አለመስጠት ፤
6. የብሎክ ነዋሪዎችን ጥቆማ መሰረት አድርጎ ማስተካከያ አለማድረግና ጥቆማውን ለሚመለከተው አካል አለማሳወቅ፤
7. በሚመለከተው የመንግስት አካልና የብሎክ ካውንስል መረጃ ሲጠየቅ አለመስጠት፤
8. ሀሰተኛ የተዛባ መረጃ ማሰራጨት፤
9. መሰረተ ልማት ላይ የደረሱ ጉዳቶችን በወቅቱ አለማሳወቅ፤
10. የሥራ ርክክብ በመዝገብ አለማድረግ፤

11. የተበላሹ ወይም የጠፉ የህዝብና የመንግስት ንብረቶችን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል አለማሳወቅ፤
12. የብሎክ ነዋሪዎችን ሰብዓዊ ክብር የሚነካ ቃላት መሳደብ፤
13. ለጥበቃ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን በአግባቡ አለመያዝ፡፡
14. የተመደበበትን ስራ አለመስራት ወይም በተደጋጋሚ መቅረት፤
15. በሥራ ቦታ ላይ አስካሪ መጠጦችን በተደጋጋሚ ጠጥቶ ሰክሮ መገኘት፤
16. የተረከበውን የብሎክ ነዋሪው ንብረት በተገቢው ያለመጠበቅ፤
17. በሥራ ቦታ ላይ ሁከት መፍጠር፤
18. የብሎክ ነዋሪውን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል መረጃ መስጠት፤
19. ጾታዊ ትንኮሳ መፈጸም፤
20. እምነት ማጉደል፤
21. ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት፤
22. በሥራ ቦታ ወይም ከሥራ ቦታ ውጪ ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈፀም፤
23. አደገኛ እፅ መጠቀም፣
24. ሌሎች የወንጀል ተግባራት ላይ መሰማራት፤

## 10. በተከለከሉ ተግባራት ላይ መሰማራት የሚያስከትለው ውጤት

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 9 ከንዑስ 1-13 ላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ፈፅሞ የተገኘ በአካባቢ ጥበቃ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ከድርጊቱ እንዲቆጠብ ወይም እንዲያስተካክል ይደረጋል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 9 ከንዑስ 14-24 ላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ፈፅሞ የተገኘ በአካባቢ ጥበቃ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ከስራው እንዲሰናበት ወይም ስራውን እንዲያቆም ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ 1 ላይ የተጠቀሰው እርምጃ በብሎክ ካውንስል ሰብሳቢ የሚወሰድ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ 2 ላይ የተጠቀሰው እርምጃ በወረዳ ብሎክ ካውንስል ሰብሳቢ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

## 11.የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

1. በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሳተፍ ሰው በስራ ሂደት ወይም በዚህ መመሪያ አንቀፅ 10 በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ እና ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

2. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጥንቅር የወረዳው የቅሬታና አቤቱታ መልካም አስተዳደር ቡድን ይሆናል፡፡

3. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የቀረበለትን ቅሬታ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በ7 የሥራ ቀናት ውስጥ አጣርቶ ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

4. የወረዳው ዋና በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን የቅሬታ የውሳኔ ሀሳብ በደረሰው አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሀሳቡን በማጽደቅ ወይም በማሻሻል ወይም በመሻር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል አራት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 12.የብሎክ ካውንስል ኃላፊነት

1. በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች መለያ መስፈርት ማዘጋጀት፤
2. በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት በጥበቃው ላይ የሚሳተፉትን መለየት፣
3. በአካባቢ ጥበቃ ላይ የተሳተፉ ሰዎችን መከታተል፣ በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው ውጭ የሆነ ተግባር ወይም ጥፋት ሲፈፀም ማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣
4. የስጋት ቦታዎችን መለየትና ማስተካከያ እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፤
5. ከጸጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት በአካባቢ ጥበቃ ላይ ለሚሳተፉ ሰዎች ስምሪት መስጠትና ክትትል ማድረግ፤
6. የአካባቢ ጥበቃ አባላት በስራው ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
7. ለአካባቢ ጥበቃዎች ለሥራ የሚገለገሉበት ግብአቶችን ማቅረብ፤
8. ከጥበቃዎች የሚመጡ ጥቆማዎችን ከሚመለከተው አካላት ጋር በመቀናጀት መፍታት፤
9. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለአካባቢ ጥበቃ የሚሆን የጥበቃ ማማ መስሪያ ቦታ ማመቻቸትና እንዲሰራ ማድረግ፤
10. በአካባቢ ጥበቃ ላይ ለተሳተፉ ሰዎች ማበረታቻ ክፍያ ከህብረተሰቡ መዋጮ እንዲፈፀም ያደርጋል፤

### 13. የክትትል ኮሚቴ ጥንቅር እና ኃላፊነቱ

1. በወረዳ ደረጃ በህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አማካኝነት የክትትል ኮሚቴ ይቋቋማል፤
2. የኮሚቴው ጥንቅር በሚከተለው መልኩ ይሆናል፡፡

ሀ/ በወረዳው በህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት የደንብ መተላለፍና ቅድመ መከላከል ቡድን መሪ.....................ሰብሳቢ፤

ለ/ የወረዳው የሰላምና ፀጥታ ጽህፈት ቤት ተወካይ......ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ/ የወረዳው የብሎክ ካውንስል ሁለት ተወካይ .........................አባል፤

መ/ የወረዳው የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ኃላፊ...............ጸሐፊ፤

3.የተቋቋመው ኮሚቴ በወረዳ ደረጃ የአካባቢ ጥበቃ አባላት ስራ እንቅስቃሴ እና ስነ ምግባር ሁኔታ እየተከታተለ ለወረዳው የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ላይ በተደነገጉት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 15. መመሪያውን ስለማሻሻል

ኮሚሽኑ ይህን መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

### 16. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በኮሚሽኑ ድረ- ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ 2016 ዓ.ም.**

ኮሚሽነር አብርሃም ታደሰ

የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ

ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር